**Seattle** Office of Labor Standards

# *የማህበረሰብ ጠበቃ እና የወንጀል ተጠቂዎች መብቶች ማስታወቂያ ለሰራተኞች*

የሆቴል ሰራተኞችን ከትንኮሳ ወይም ከጥቃት ድርጊቶች የመጠበቅ ድንጋጌ፣ የሲያትል ሙኒሲፓል ኮድ (The Protecting Hotel Employees from Harassing or Violent Conduct Ordinance, Seattle Municipal Code (SMC)) 14.26 ሆቴል እና የዲጋፍ ሆቴል ንግድ ይህንን ማስታወቂያ ሽፋን ለተሰጣቸው የጥቃት ወይም የትንኮሳ ባህሪ ድርጊት በሆቴል እንግዶች ላደረሰባቸው ሰራተኞች ማቅረብ አለባቸው ።

**በሆቴል እንግዳ የጥቃት ወይም የአደጋ ተጋላጭ ከነበሩ፣ የሚከተሉት መብት አልዎት፡-**

1) ***የማህበረሰብ ጠበቃ።*** የማህበረሰብ ጠበቃ ሚና ነፃ ሚስጥራዊ የጥብቅና አገልግሎቶችን በማንኛውም ሰዓት እና በማንኛውም የሳምንቱ ቀናቶች ለእርስዎ ማቅረብ ነው። የማህበረሰብ ጠበቃው የሚከተሉትን የድጋፍ አገልግሎቶችን ይሰጣል፡ ሀ) በ SMC 14.26 መሠረት መብቶችዎን እና ለተግባር እርምጃ ያለዎትን አማራጮች ያብራራል፣ ለ) የእርስዎን የግል ፍላጎቶች ለማሟላት የሪፈራል አገልግሎቶችን መስጠት፣ እና ሐ) ሪፖርት ለማድረግ ከመረጡ፣ በሆቴል እንግዳ የሚደርስብዎትን የጥቃት ወይም የትንኮሳ ተግባር ድርጊትን ሪፖርት ለማድረግ እርስዎን ማገዝ። ለእነዚህ አገልግሎቶች ያለዎት ተደራሽነት/ተጠቃሚነት የእንግዳ ሥነ ምግባር የጎደለው ድርጊት ሪፖርት በማድረግ ላይ የተመሠረተ አይደለም፤ አማራጮችዎን ለመገምገም ብቻ እነዚህን አገልግሎቶች ሊያገኙ ይችላሉ።

   የሲያትል ከተማ እነዚህን ሀብቶች ለእርስዎ ለማቅረብ ከ King County Sexual Assault Resource Center (KCSARC) ጋር፣ ከማህበረሰብ-ተኮር ፣ የተጎጂዎች ተሟጋች ድርጅት የ 24 ሰዓት የቀጥታ መስመር ኮንትራት ተፈራርሟል። ሚጽጥራዊ አገልግሎቶችን ለማግኘት ለ KCSARC በሚከተለው ቁጥር መደወል ይችላሉ፡- 1-888-99-VOICE (1-888-998-6423)። ስለ KCSARC የበለጠ ለማወቅ፣ እባክዎን፡- https://www.kcsarc.org/ ይጎብኙ።

2) ***በ RCW 7.69.030 መሠረት የወንጀል ተጠቂዎች ጠበቃ እና ሌሎች መብቶች*** በተሻሻለው የዋሽንግተን ሕግ (Revised Code of Washington (RCW)) 7.69.030፣ የወንጀል ተጠቂዎች በወንጀል ፍርድ ቤት ወይም በልዩ ፍርድ ቤት ችሎት ላይ ተፈፃሚነት ያላቸው በርካታ መብቶች ይሰጣቸዋል፡፡ የጥቃት ወይም የወሲብ ወንጀሎች የተረፉ ከሆኑ በየክስ አቃቤ ህግ ወይም የመከላከያ ቃለመጠይቆች ጊዜ የወንጀል ተጠቂ ጠበቃ የማቅረብ መብት አልዎት፡፡ የወንጀል ተጠቂ ጠበቃ ሚና ስሜታዊ ድጋፍ እንዲሰጥዎት ነው። በ RCW 7.69.030 መሠረት፣ እርስዎ በፍርድ ችሎት ምክንያት ክፍያን ማጣት ለመቀነስ አስፈላጊ ከሆነ በአፋጣኝ የህክምና እርዳታ እንዲያገኙ እና አስፈላጊ ከሆነ አንድ ሰው ከአሰሪዎ ጋር ጣልቃ እንዲገባ የማድረግ መብትም አልዎት፡፡ ከወንጀል የተረፉ ሰዎች የተሰጡትን መብቶች በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት RCW 7.69.030 ን ይመልከቱ፡፡

   ስለ የወንጀል ተጠቂዎች አገልግሎቶች የበለጠ መረጃ ለማግኘት የሚከተለውን ሊያነጋግሩ ይችላሉ፡ Victim Support Services በ 1-888-288-9221 ወይም KCSARC በ 1-888-998-6423።

3) ***ኪንግ ካውንቲ ልዩ ጥቃት ፕሮቶኮል (King County Special Assault Protocol)።*** ይህ ፕሮቶኮል በኪንግ ካውንቲ ውስጥ የተወሰኑ ወንጀሎችን በሚመለከት ጉዳዮች ለትብብር ምርመራዎች መመሪያዎችን እና አገልግሎቶችን ይሰጣል፡፡ ፕሮቶኮሉ የምርመራዎችን ታማኝነት ለማሻሻል፣ የተጎጂዎችን፣ የተጠርጣሪዎችን እና የማህበረሰቦችን ጥቅም ለመጠበቅ፣ እንዲሁም ለተረፉ ሰዎች እና ለቤተሰቦቻቸው ተገቢ አገልግሎቶች መኖራቸውን በማረጋገጥ በ RCW 26.44.180 እና RCW 26.44.185 መሠረት ተቋቁሟል፡፡

*ስለዚህ ቅጽ ጥያቄ ያላቸው አሰሪዎች እና ሰራተኞች የሠራተኛ ደረጃዎች ጽ/ቤት (Office of Labor Standards (OLS)) በ 206-256-5297 ማነጋገር ወይም የ OLS ን ድህረ-ገጽ http://www.seattle.gov/laborstandards ይጎብኙ።*

**እትም፡- 07/2020**